<u>ሞት ላይቀር ማንቋረር</u>

ሰው ሰው መሆኑን ምነው ይዘነጋል
እውነትን በውሸት ለምን ይለውጣል
ማንነት ረስቶ እንዴት ይኮፈሳል
ሁልጊዜ በእብሪት መጠራት ይመርጣል
ጽዋው የሞላ ለት የግድ ይጨለጣል።

ቅር … ቅር … ቅር …
ሞት ላይቀር ማንቋረር

ሽረኛዋ ልቤ ፈርታ መርበትበቷ
ሞትን ሳታቅ ኖራ እንድህ መረታቷ
ባለጌዋ ምላስ ተዘግታ መቅረቷ
ያቺ ዓይነ ደረቅ ቅንድቧ ተሰብሮ ደክማ መቃተቷ
እዚህ እዚያ ያለን ቀረ መመልከቷ።

ቅር … ቅር … ቅር
ሞት ላይቀር ማንቋረር

ዋይ የፀፀት እንባ ዓይ አወራረዱ
ጥንድ መንታ ሆነው አንድላይ ወረዱ
ያ የበደል ስንቅ የነዳማ ለቅሶ
ዳግም ላይመለስ ሄደ ጥርሱን ነክሶ
ዓለምን ላያያት በዚህ ተመልሶ ።

ቅር … ቅር … ቅር
ሞት ላይቀር ማንቋረር

ልቤ ትቢተኛ
ምላሴ ነውረኛ
መጥፎ ነገረኛ

የክብሬ ምቀኛ
ድቤ አወረዱኝ አርፌ ልተኛ።

ሞት ላይቀር ማንቋረር
ቅር ... ቅር ... ቅር
ሞት ላይቀር ማንቋረር
ቅር ... ቅር ... ቅር ...ቅር ........... .... .. .

ለእኔ ለራሴ መለስ

ሐምሌ 2004